# ሰካራሙ...

ቤቴ እንደመተኛት፣ ከሚስቴ ተቃቅፎ
ስጠጣ ኣምሽቼ፣ እኩለ-ሌት ኣልፎ
ኣንጀቴ ተስቧል ከማስታወክ ተርፎ
ናላየም ጠምብዟል፣ ኣየ! ስካር መጥፎ...

ኣይጥና እሽኮኮ በተንኮል ኣሟርተው
በውድቅት ሌሊት በኔ ተሰማርተው
በምን ምትሓት ይሆን ከኣልጋየ ገብተው...

ከዚህና ከዚያ ዘልለው ሲቦርቁ
በግራና በቀኝ ዳንስ ሲደልቁ
በእግሮቼ መኻል ሲያፌዙ፣ ሲስቁ!
እንዴት ልያዛቸው በቅርቡ፣ በሩቁ...

ታንኳ ላይ ነኝ ያለሁ? ባሕር ላይ ነኝ ልበል?
ታድያ ከየት መጣ ውቅያኖስ ማዕበል?
ኣየ ኣጉል ስካር፣ ኣየ! መጥፎ ኣመል...

ኣወይ መጨማለቅ፣ ምን ጭቃ ሳቦካ?
የባሕሩስ ጥልቀት እንዴት ነው እሚለካ?
የምን እርጥበት ነው እጄስ የሚነካ?
የፈጠርኸኝ ጌታ! ሸንቻለሁ ለካ...

ገ/ኢ. ጐርፉ።